
# የስድስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የሞዴል ፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

## ቁጥር ሶስት

1. ከሚከተሉት ውስጥ አንፃራዊ መገኛን የማይገልፀው የቱ ነው ?

   ሀ) ሰሜን   ለ) ደቡብ   ሐ) ምስራቅ   መ) ኬንትሮስ




2. ከላይ በንስሉ ላይ ፊደል "ሀ" ን የሚወክለው ኡብይ ትይዩ መስመር ምን ይባላል ?

   ሀ) የአርክቲክ ክበብ   ሐ) የምድር ወገብ

   ለ) የአንታርክቲክ ክበብ   መ) የካንሰር መስመር

3. ከላይ በምስሉ ላይ የምድር ወገብን የሚያመለክተው የቱ ነው ?

   ሀ) ሠ   ለ) መ   ሐ) ሐ   መ) ለ

4. ከሚከተሉት ውስጥ በቋሚ መስመሮች መካከል ያለውን ማዕዘናዊ ርቀት ለመለካት የምንጠቀምበት የሃሳብ መስመር ምን ይባላል ?

   ሀ) የኬክሮስ መስመር   ሐ) የኬንትሮስ መስመር

   ለ) ሰያፍ መስመር   መ) ዝግዛግ መስመር

5. በአፍሪካ ካርታ ላይ የኢትዮጵያን ፍፁማዊ መገኛን የሚገለፀው የቱ ነው ?

   ሀ) ከ $12^0$ እስከ $18^0$ ሰሜን ኬክሮስ እና ከ 36 22 ምስራቅ ኬንትሮስ

   ለ) ከ $3^0$ - $15^0$ ሰሜን ኬክሮስ እና ከ $33^0$ - $48^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

   ሐ) ከ $12^0$ ሰሜን ኬክሮስ እና ከ $41^0$ - $51^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

   መ) ከ $12^0$ 19 ሰሜን ኬክሮስ እና ከ $43^0$ - $44^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

LIVEWORKSHEETS

6. በካርታ ወይም በሉል ላይ ከምስራቅ ወደ ም ዕራብ ወይም በተቃራኒው የተሰመረ የሀሳብ መስመር ምን ይባላል ?

ሀ) ግሪንዊች ሜሪዲያን ሐ) ቋሚ መስመር

ለ) የኬንትሮስ መስመር መ) የኬክሮስ መስመር

7. በካርታ ወይም በሉል ላይ ከምድር ወገብ በስተሰሜን ስንት ትይዩ መስመሮች ይገኛሉ ?

ሀ) 90 ለ) 180 ሐ) 60 መ) 360

8. ኢትዮጵያን በስተሰሜን በኩል የሚያዋስናት የምስራቅ አፍሪካ ሀገር መን ይባላል ?

ሀ) ኬን ያ ለ) ጂቡቲ ሐ) ኤርትራ መ) ሶማሊያ

9. ከሚከተሉት ውስጥ የአፍሪካ ቀንድ ሀገር ያልሆነው፡-

ሀ) ጂቡቲ ለ) ግብጽ ሐ) ሶማሊያ መ) ኢትዮጵያ

10. ከሚከተሉት ሀገራት መካከል የባህር በር ያለው ሃገር የቱ ነው ?

ሀ) ማላዊ ለ) ኢትዮጵያ ሐ) ሩዋንዳ መ) ማዳጋስካር

11. ከሚከተሉት የምስራቅ ተራራዎች መካከል በ እሳተ ገሞራ ፍንዳታ ያልተፈጠረው የቱ ነው ?

ሀ) የሩዋንዛሪ ተራራ ሐ) የኪሊማንጃሮ ተራራ

ለ) የሜሩ ተራራ መ) የኤልጎን ተራራ

12. ከሚከተሉት ውስጥ በኢትዮጵያ የማይገኘው ታዋቂ የቱሪስት መስህብ የቱ ነው ?

ሀ) የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ሐ) የብውንዲ ጥቅጥቅ ደን

ለ) የዳሎል ዝቅተኛ ቦታዎች መ) የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ

13. የማላዊ ሐይቅን በስተደቢብ በኩል የሚአያዋስነው ሀገር የቱ ነው ?

ሀ) ኬንያ ለ) ታንዛንያ ሐ) ሞዛምቢክ መ) ማላዊ

14. ከሚከተሉት ሐይቆች መካከል ከስምጥ ሸለቆ ሐይቅ ውስጥ የማይመደበው የትኛው ነው ?

ሀ) የዝቋላ ሐይቅ ሐ) የላንጋኖ ሐይቅ

ለ) የዝዋይ ሐይቅ መ) የማላዊ ሐይቅ

15. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ ወንዞች ውስጥ በታንዛኒያ እና በሞዛምቢክ ድንበር ላይ የሚገኘው:

ሀ) የገናሌ ወንዝ ሐ) የሩሹማ ወንዝ

ለ) የአባይ ወንዝ መ) የዛምቤዚ ወንዝ

16. የድንቅነሽ ( ሉሲ) ቅሪት የተገኘበት የምስራቅ አፍሪካ ሀገር የትኛው ነው ?

ሀ) ኤርትራ ለ) ኢትዮጵያ ሐ) ጂቡቲ መ) ኬንያ

LIVEWORKSHEETS

17. ከሚከተሉት መተግበሪያዎች መካከል የአንድን አካባቢ የገበያ ፅር ለመፈለግ የምንጠቀምበት መተግበሪያ የቱ ነው ?

ሀ) ጂፒኤስ　　ለ) ጎግል ኧርዝ　　ሐ) ጎግል ካርታ　　መ) ኮምፓስ

18. ትራፊኮች የመኪና አሽከርካሪዎችን በምን ያህል ፍጥነት እንደሚያሽከረክሩና የሚነዱበትን ፍጥነት ለመቆጣጠር የሚያስችለው መተግበሪያ ምን ይባላል?

ሀ) ጂፒኤስ　　ለ) ጎግል ኧርዝ　　ሐ) ጎግል ካርታ　　መ) አጉሊ መነፅር

19. ተመራማሪዎች ሩቅ ያሉ ቦታዎችን ለማየት፣ ለመመርመር እና ስለተለያዩ በሽታዎች መከሰት ትንበያ ለመስጠት ተሚጠቀሙበት መተግበሪያ ምን ይባላል?

ሀ) ጎግል ካርታ　　ለ) ጎግል ኧርዝ　　ሐ) ጂፒኤስ　　መ) ስቴቶስኮፕ

20. ኦክስጂንና አልሚ ምግቦች ለሰውነታችን ህዋሶች የሚሰራጩበት ሂደት ምን ይባላል?

ሀ) ስር አተ ልመት　　ሐ) የደም ዑደት

ለ) ስራዓተ ትንፈሳ　　መ) ሁሉም

21. ከሚከተሉት የደም ህዋሶች መካከል ኦክሲጂንን ለመሸከም የሚያስችል ሄሞግሎቢን የሚባል ህመልማል ያላቸው የትኞቹ ናቸው ?

ሀ) ቀይ የደም ህዋሳት　　ሐ) ፕሌትሌትሌትስ

ለ) ነጭ የደም ህዋሳት　　መ) ፕላዝማ

22. ከሚከተሉት ውስጥ የደም ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) አየር ማስተላለፍ　　ሐ) ደም ማርጋት

ለ) በሽታ መከላከል　　መ) ደም መርጨት

23. ከሚከተሉት የደም ስሮች ውስጥ ለሰውነታችን ህዋሶች በጣም ቅርብ የሆኑና ስስ ግድግዳ ያላቸው የትኞቹ ናቸው ?

ሀ) ደም ቅዳ　　ሐ) ቀጫጭን የደም ስሮች

ለ) ደም መልስ　　መ) ቀይ የደም ህዋሳት

24. ከሚከተሉት የልብ ክፍሎች ውስጥ በኦክሲጂን የበለፀገን ደም ከሳንባ በፑልሚናሪ ቬይን አማካኝነት የሚቀበለው የትኛው ነው ?

ሀ) ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ　　ሐ) ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

ለ) ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ　　መ) ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

25. በጉርምስና ወቅት በወንዶች ላይ ብቻ የሚታይ ስነ ህይወታዊ ለውጥ የትኛው ነው ?

ሀ) የድምጽ መጎርነን　　ሐ) ፈጣን የሆነ እድገት

ለ) የዳሌ መስፋት　　መ) የባህሪ ለውጥ ማሳየት

LIVEWORKSHEETS

26. በወር አበባ ጊዜ ከሚከሰቱ ሂደቶች መካከል አንዱ የሆነው :

ሀ) የማህፀን ግድግዳ በደም ስሮች መደራጀት

ለ) እንቁላል ከእንቁልጥ መውታት

ሐ) እንቁላል ወደ ማህፀን በር መግባት

መ) ሁሉም

27. ኦክሲጂንን ወደ ሰውነታችን ውስጥ የማስገባት እና ካርቦንዳይኦክሳይድን ወደ ውጭ የማስወጣት ሂደት ምን ይባላል?

ሀ) የደም ዑደት ለ) ልመት ሐ) አፀግብሮት መ) ትንፈሳ

28. አየር ወደ አየር ከረጢት መግቢያና መውጫ በመሆን የሚያገለግለው የመተንፈሻ አካል የሆነው :-

ሀ) ደቂቅ ትንቧ ለ) ትንክረት ሐ) ድህረ አፍ መ) ሰርን

29. ከሚከተሉት የስራዓተ ትንፈሳ ክፍሎች ወስጥ ቅርፁን በመቀያየር ሳንባችንን በትክክል እንዲተነፍስ የሚያስችለው :-

ሀ) ሰርን ለ) የአፍ ወና ሐ) ድልሺ መ) ትንክረት

30. የምጋትና የ ኢ- ምጋት የአየር ምንዝሮች በመቶኛ ሲቀመጡ መጠኑ የማይለዋወጠው የትኛው ነው ?

ሀ) ኦክሲጂን ሐ) ካርበንዳይ ኦክሳይድ

ለ) ናይትሮጂን መ) የውሃ ትነት

31. ከሚከተሉት ልዩ ቁሶች መካከል ድብልቅ የሆነው የትናው ነው ?

ሀ) ውሃ ለ) ስኳር ሐ) ጨው መ) ወተት

32. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የዋህድ ዘር ድብልቅ ምሳሌ ነው ::

ሀ) ወተት ለ) አየር ሐ) የጤፍና የስንዴ ድብልቅ መ) ደም

33. የጨው ሙሙት በውስጡ ስንት ምንዝሮች ይዟል?

ሀ) 3 ለ) 5 ሐ) 2 መ) 1

34. ከሚከተሉት ውስጥ ልይ ዘር ድብልቅ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) የዘይትና የውሃ ድብልቅ ሐ) ለስላሳ መጠጦች

ለ) የአልኮል እና የውሃ ድብልቅ መ) የሙዝ እና የቅቤ ድብልቅ

35. የልዩ ቁሶች ድብልቅ ባላቸው የእፍግታ ልዩነት አማካኝ ነት የምንለይበት የድብልቅ

መለያ ዘዴ ምን ይባላል ?

ሀ) ንጥረት ሐ) ቀረራ

ለ) ትነት መ) ጥልያ

LIVEWORKSHEETS

36. የሚሙ ጠጣሮችን ከአሚሚው ፈሳሽ የምንለይበት የድብልቅ መለያ ዘዴ የቱ ነው ?

ሀ) ንጥረት　　　　ሐ) ጥልያ

ለ) ትነት　　　　መ) ቀረራ

37. ከሚከተሉት የጉልበት ምንጮች ውስጥ አንዱ ኢ-ታዳሽ የጉልበት ምንጭ ነው።

ሀ) የውሃ ጉልበት　　　　ሐ) የነፋስ ጉልበት

ለ) የፀሃይ ጉልበት　　　　መ) የተፈጥሮ ነዳጅ

38. አንድ አካል በከፍታ አማካኝነት የተነሳ ሊኖረው የሚችለው የጉልበት አይነት ምን ይባላል?

ሀ) የክህሎት ጉልበት　　　　ሐ) የእንቅስቃሴ ጉልበት

ለ) የኤሌክትሪክ ጉልበት　　　　መ) የመሬት የስበት ሃይል

39. ዳቦን ለመቁረስ ይስሚያስችል የቀላል መኪና አይነት የትኛው ነው ?

ሀ) መፈንቅል　　　　ሐ) ሽብልቅ

ለ) መፍቻ　　　　መ) ሽክርክሪት

40. ፎቅ የሚገነቡ ባለሙያዎች ቁሳቁሳቸውን ፎቅ ላይ ለማውጣት የሚጠቀሙበት

የቀላል መኪና ዓይነት መን ይባላል?

ሀ) ሽክርክሪት እና ዘንግ　　　　ሐ) ሽክርክሪት

ለ) ዘንበይ ወለል　　　　መ) መፈንቅል

LIVEWORKSHEETS